# አጫጭሰውና!

ጠንክር ጌቻሞ / ከዲላ

ስንት አመት ይቆዝም ስንት አመት ይጠብቅ፣

ስንት አመትስ ይሙት ስንት አመት ይታዘን፣

አጫጭሰውና እርጥቡን ከደረቅ፣

እዚያው ጭሶ ጭሶ እዚያው ነዶ ይለቅ።

ባዩ ሰው ቢበዛ አናዳጁም ሰው -

ቀላል እኮ አይደለም ምክር መቀበሉ፣

ሁሉን ነገር ላዩ ዕድሜ ለታደሉ።

በስሜት ተገፍቶ የሚሰራ ስራ፣

ሲሆን ተስተውሏል ተራ አጉል ፉከራ።

ይኸን የሰበካ መንገድ የመረጡ፣!

ፈታኝ ቀን ሲመጣ ታይተዋል ሲሮጡ።

ምን መሮጡ ብቻ!

አዝለውም ታይተዋል የወሬ ስልቻ።

ፍሬ አልባ ሆነ እንጂ ፍሬ ቢኖረው፣

እነ አያ ቸፍ ቸፍ  ያደረሱት ጥፋት ወደርም የለው።

አጫጭሰው ይንደድ እንደ ዕጣን ብርጉድ፣

በሚሉት ፈሊጥ!

ዝም ብሎ አይማግዱም እርጥቡ እንዲነድ፣

እርግጥ ነው በዘዴ ለይቶ አስቀምጦ -  ሸንሸኖ ሸንሸኖ፣

ጭራሮን ሰባብሮ ቁመቱ ማጠሩን መድረቁን አጢኖ፣

በፍንግርግርነት – ጠላት ሲመኘው፣

አንድዶ መሞቁ የማይሳት ነው።

ግና! ባስመሳዮች አቲሆ ባቲሆ!

ታጋይ ጦር ጦር አይልም በፉከራ ጮሆ!

አንዲት ጥይትና አንድ ሰው እስኪቀር፣

የሚለው ድንፋታ! በእግሬ አውጭኝ ሲቀየር።

ታይቷል ተመስክሯል የፋሽስቶች ጉራ፣

ሳዳም ከጉራንጉር - ጋዳፊ ድልድይ ስር

መንግስቱ ፍርጠጣ - ነፍስ ቋጥሮ በረራ።

ዱላ ወይስ መላ - ያሉት ተገልብጠው የዱላ ጠበቃ ሲሆኑ ነን ሲሉ፣

አሳይቷል ጊዜው አሳይቷል ትግሉ።

የቀበሌው ካድሬ - የታሪክ አዋቂ አርጎ ቆጥሮ እራሱን፣

ወሬ ሲተበትብ የባጡን የቋጡን፣

መስካሪና አዋቂ መገኘቱን በቅርብ ስለማይፈልገው፣

ኢህአፓ ገዳይ ነው፣

ኢህአፓ ያገር ጠላት! ከወያኔ አንድ ነው።

ምንትስ ምንትስ ሲል መወሻከቱ፣

ሀሰት ለማለት ነው የሰራውን ሁሉ

ያደባባይ ምስጢር - በግልፅ የሚያውቀውን ሁሉም በየቤቱ።

ለፍብረካው ስራ ደጋፊ ለማግኘት፣

የበግ ለምዱን ለብሶ ተኩላ አለ በበረት፣

ቀን ቀን ከህዝብ ጋር - ሌት ከወያኔ ቤት።

## እንደዚህ እያለ

ጥሩ በጎ ነገር ላገር ለወገን፣

እንደምን እንስራ ኢህአፓ አግዶን።

ሁላችን ተባብረን ኢህአፓ ላይ ብንዘምት፣

አንሰማም ነበረ የቀይ ሽብር ዕልቂት።

እጅ እጅ የሚያየዉን በገንዘብ አማለን፣

ብንይዘው ጠፍረን ከትግል አግልለን፣

ስለ ኢህአፓ የሚዘከሩትን ድረገፅ በሙሉ፣

ቢያንስ ማዳከሙን ብንችል ተረዳድተን - እንዲጠፉ ምስሉ፣

ዲሞክራሲያ፣ አሲምባ፣ ደብተራው፣ ፍኖተ

የሚባሉት ሁሉ የሚረጩትን መርዝ፣

ከወያኔ ካዝና ትንሽ ብንታገዝ፣

አያቅትም ነበር ገድሉን ለማደብዘዝ።

ግን ብቻ ለብቻ!

ትርፉ ውርደት ይሆናል - መሆን መዛበቻ።

ከወያኔ ጋራ በሰላም ተቀምጠን ኑሮአችን እናዳንኖር

ያደረገን ማነው? ለህዝብ እያሳጣ፣

ወይ እኛ እንተወው! ወይ ኢህአፓ ያቁም ከዕይታችን ይውጣ!

በፖለቲካው ውስጥ የኛ አጉል መዳከር - እሱ እስካለ ድረስ ምንም አይዋጣ!

ብለው ሲዶልቱ ሲያሴሩ በደባ፣

አላወጣ ብሎ ሲያስቸግር ሁኔታው-

ነገር ሲጠነክር ይላሉ እንደገና ኢህአፓ የት ገባ?

ኢህአፓ እንዳይኖር እየታገላችሁ፣

በራሳችሁ መቆም ዘዴው ሲጠፋችሁ፣

ዘዴውን መላውን ማወቅ ሲሳናችሁ፣

ከህዝብ ለማራቅ ሲከሽፍ ሙከራችሁ

አንድ ነን እምነቱ ላይቀር ጥያቄአችሁ፣

ከየት የመጣ ነው፣ ሰፊዋን ኢትዮጵያ አጥብቦ ማየቱ፣

ከጠባብ ወግኖ ወገንን ማጥቃቱ።

ከየት የመጣ ነው?

ስለዚህ ወገን ሆይ! ኢህአፓን ከህዝብ ውስጥ ማውጣት አይቻልም፣

አታርጉት ኢላማ! ደርግ ሞክሮት ከሽፏል፣

አንጃ ብዙ ጊዜ ተነስቶ አፍሮበታል።

ወያኔን ጠቅላላ -  በዚህ የተነሳ  የራስ ምታት ህመም /ሚግሬን/ ጨርሶታል።

ኢህአፓ ሲነሳ ዋለልኝ ሲነሳ፣

ጸጋዬ ደብተራው ተስፋዬም ሲነሳ

ፋሲካ ሲባልም ኢያሱ ሲነሳ

የሚያማቸው ካሉ አበጀን ታዲያሳ!

በፅናት እኮ ነው በአመራር ብቃት፣

የሀቅ ማተብ ገምዶ ፀንቶ በመስራት።

ጀግናው የኢሕ አፓማ

ሳያጓጓው ሀብቱ፣ ሳይማርከው ብሩ፣

ደልቶት መኖር ሲችል -  ታማኝ ሆኖ ዘልቆ ለህዝቡ ሳገሩ፤

ከወገን ተጣብቆ በስቃይ መኖሩ።

አንዳንዱ ተልካሻ፣

ሰድስት ወርም አይችል እንኳንስ ዕድሜ ልክ -

ህዝብን ለማገልገል አርጎ የስራ ድርሻ።

አርአያ በመሆን ግንባሩን ሳያጥፍ ለፋሽስት ለባንዳ፣

ትግሉ ነው ህይወቴ፣ ቢንቆረቆር ደሜ፣

እያለ ዘምሮ ወለም ዘለም ሳይል እሱ እየተጎዳ፣

ትግል ወንጀል ሆነ ታጋይ ቢያሰናዳ?

አብዛኛው አባሉ ያልተገላበጠ በጽናት የኖረ፣

በጥቃት ያረረ፣

በኩራት የሞተ፣

በጉራና በቁንጥ - ልቡ ያልታበተ፣

ላገር ለወገን ሲል - ተቆራምዶ የኖረ በትግሉ ያሸተ።

ከቶ እንደ ኢህአፓ ማን አለ እሚታመን፣

ህዝብን ሙጥኝ ያለ - መከራና ችግር የማይረታው ሀዘን?

ከየልቦናችን ከቀልባችን እንሁን፣

ትርምሱን ትተን - እንታገል ትግሉን።

**ቢያደነጋግርም - ቢመስል የማይሆነው፣**

**ልባችን አይዋዥቅ ህዝብ አቸናፊ ነው፣**

**እያለ እሚመክር፣**

**ወኔ ነው ኢህአፓ ይኑርልን ላገር ይኑርልን ለክብር!!**

//////////--------/////////